በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

## የስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም ማኑዋል ቁጥር001/2009 ዓ.ም/ረቂቅ/

ሰኔ 2009

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

ማውጫ ........................................................................................................................................... I

መግቢያ ........ 1

ክፍልአንድ ........ 2

አጠቃላይ ........ 2

1. ዓላማ ........ 2

2. ትርጉም ........ 2

3. መርሆዎች ........ 4

ክፍልሁለት ........ 5

2.1 የስራፈላጊዎችልየታ፣አመዘጋገብእናየግንዛቤፈጠራ ........ 5

2.1.1 ስራፈላጊዎችልየታናምዝገባአስፈላጊነት ........ 5

2.1.2 የስራ ፈላጊዎች ልየታ ........ 5

2.1.2.1 የስራፈላጊዎችለመለየትየሚከናወኑተግባራት ........ 5

2.1.3 የስራፈላጊዎችአመዘጋገብ ........ 8

2.1.3.1 የከተማነዋሪየሆኑየሥራፈላጊዎችአመዘጋገብ ........ 8

2.1.3.2 የከተማነዋሪየሆኑናመታወቂያየሌላቸውሥራፈላጊዎችአመዘጋገብ ........ 8

2.1.3.3 የከተማነዋሪያልሆኑስራፈላጊችአመዘጋገብ፣ ........ 8

4.4 የስራፈላጊዎችመመዝገቢያወቅት ........ 9

4.6 የስራፈላጊዎች ምዝገባአፈጻጸምሪፖርት አቀራረብ ........ 9

4.7 የስራፈላጊዎችየግንዛቤፈጠራ ........ 10

4.8 የስራፈላጊዎችየአጫጭርየስራአመራርእናክህሎትስልጠና ........ 10

ክፍልሶስት ........ 10

5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችአደረጃጀትእናየስራዕድልፈጠራአማራጮች ........ 10

5.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችአደረጃጀትአማራጮች ........ 10

5.1.1 የአደረጃጀትዓይነቶች ........ 11

5.1.1.1 በግልየሚቋቋምኢንተርፕራይዝመስፈርት ........ 11

5.1.1.2 የንግድማህበርአደረጃጀትዓይነቶችናመሥፈርት ........ 11

5.1.1.3 በንብረትሽርክናማኀበርአደረጃጀትናመስፈርት ......11

5.1.1.4 ኃላፊነቱየተወሰነየግልማኀበር ......12

5.1.3 የተደራጁኢንተርፕራይዞችሪፖርትአደራረግ ......13

5.2 የስራዕድልፈጠራመንገዶች ......13

5.2.1 በመደራጀትየሚፈጠርየስራዕድል ......13

5.2.2 በቅጥርየሚፈጠርየስራዕድል ......13

5.3 የስራዕድልፈጠራሪፖርትአደራረግጥንቃቄማድረግየሚገቡጉዳዮች ......14

ክፍልአራት ......15

2. የባለድርሻአካላትሚና ......15

11. የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የሚያስባብሩ አካላት ተግባርና ሀላፊነት፣ ......19

12. የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ......20

ክፍልአምስት ......23

3. የድጋፍ ክትትል እና ግብረ መልስ አግባብ ......23

7.1 ሪፖርት ......23

7.1.1 የወርሃዊሪፖርትአቀራረብ፣ ......23

7.1.2 የሩብዓመትዕቅድክንውንሪፖርትአቀራረብ፣ ......23

7.1.3 ዓመታዊየዕቅድክንውንሪፖርትአቀራረብ ......24

7.2 የአካል ......24

7.3 የመስክላይክትትል ......24

8. የተፈጻሚነት ወሰን ......25

9. ማኑዋል ስለማሻሻል ......25

10. ማኑዋሉስለሚጸናበትሁኔታ ......25

አባሪዎች ......26

## መግቢያ

በከተሞች የተንሰራፋውን ድህነትና ስራ አጥነትን በመቅረፍ የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነትን ለማስፈን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ዋነኛው መሳሪያ በመሆኑ መንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርጾ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በተደረገ ርብርብ ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ሀገር እየጨመረ የመጣውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን እንዲሁም የሌሎች ስራ ፈላጊዎችን ቁጥር በተቀናጀ መልኩ በስራ ፈላጊነት በመመዝገብ ባሉት የስራ ዕድል አማራጮች ወደ ስራ ለማስገባት እንዲቻል የድጋፍ አሰጣጥ አግባቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመነሻነትም የስራ ፈላጊ ልየታ አፈጻጸም በ2004 በጀት አመት የተዘጋጀውን የስራ ፈላጊዎች አመዘጋገብ ጋይድ ላይን መሰረት በማድረግና የሰራ ዕድል ፈጠራው የሚመራበት አግባብ ደግሞ በ2008 በጀት አመት በተዘጋጃው ማንዋል በመውሰድ ሲሆን ስራ ፈላጊዎችን ከምዝገባው እስከ ስራ ዕድል ፈጠራው በምን አግባብ መፈጸም እንዳለበት ከማሳየትና በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ከታዩ ማነቆዎች አንዱ በየደረጃው የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ወጥ ባለመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ጥራት ያለው የስራ ፈላጊዎች ምዝገባ እና የስራ ዕድል ፈጠራው መረጃ አያያዝ ስርዓት ወጥነት እንዲኖረው የሚያስችል የተሻሻለ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

### 1. ዓላማ

በስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ወጥነት ባለው ስርዓት እንዲመራ ለማድረግ ነው፡፡

### 2. ትርጉም

1. "***የአንድ ማዕከል አገልግሎት* መስጫ ጣቢያ**"ማለት የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሕጋዊነትን ለማስፈን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የመንግስታዊ ድጋፎችና አገልግሎቶች በተቀናጀ መልኩ ከአንድ ስፍራ በአንድ አስተባባሪ አካል ሥር ካሉ አካላት የሚያገኙበት አደረጃጀት ነው፡፡
2. "**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47/1/ የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ ማንዋል አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፡፡
3. "**ከተማ**" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት እና 2 ሺህ ወይም ከዚህ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡
4. "**የክልል ኤጀንሲ ወይም ቢሮ**" ማለት በየክልሉ የተዋቀሩ የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሥራን የሚደግፍና የሚያስተባብር አካል ነው::
5. "**ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ**"ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት እና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራናየካፒታል መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡
6. "**አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ**" ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት እና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የካፒታል መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሽህ) ወይም በከተማ ግብርና፣ በባህላዊ ማዕድን ማምረትና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ 1.5 ሚሊዮን ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

7. **“ነባርኢንተርፕራይዝ”** ማለትሕጋዊሰውነት ወይም ፈቃድ አግኝተው አንድዓመትእናበላይየሞላቸውሲሆኑሲቋቋሙየተሟላ ወይም /በከፊልየድጋፍአገልግሎትያገኙናቸው።

8. **“አዲስኢንተርፕራይዝ”**ማለትበኢንተርፕራይዞችአደረጃጀትመሠረትሕጋዊፈቃድአግኝተውወደሥራ ከተሰማሩአንድዓመትያልሞላቸውሲሆኑሲቋቋሙየተሟላወይምበከፊልየድጋፍአገልግሎትያገኙናቸው።

9. **“ስራ ፈላጊዎች”** ማለት ዕድሜያቸው 18 እስከ 60ዓመት የሆናቸው፣ የመሥራትፍላጐትናችሎታእያላቸው የራሳቸውንሥራበመፍጠርምሆነበመቀጠርቋሚየሥራመስክየሌላቸው፤ያልተማሩትንናበተለያየት ምህርትደረጃየሚገኙ የሀገሪቱዜጐችናቸው።

10. **“የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅምሩቃንስራፈላጊዎች”**ማለትከመንግስትናከግልዩኒቨርሲቲዎችበዲግሪናከዚያበላይ፣ከመንግስትናከግልኮሌጆች፣የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናተቋማትከደረጃ I-V የተመረቁና የመስራት ፍላጎትና ችሎታ እያላቸውየራሳቸውን ሥራ በመፍጠርም ሆነ በመቀጠር ቋሚ የሥራ መስክ የሌላቸውየሀገሪቱ ዜጎች ናቸው።

11. **“የሥራ ዕድል ፈጠራ”** ማለት የመስራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ስራ ያልገቡ ዜጎችን በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የስራ ዘርፎች ማሠማራት ነው።

12. **“ቋሚየሥራዕድል”**ማለትየራሳቸውንኢንተርፕራይዝፈጥረውየሚሰሩወይምበሌሎችድርጅቶችውስጥከአንድዓመትላላነሰጊዜ በቋሚነት ተቀጥረውበፔይሮልክፍያበማግኘትየሥራዕድልየተፈጠረላቸውማለትነው::

13. **“ጊዜያዊየሥራዕድል”**ማለት በጥሪት ማፍሪያ ፕሮጀክቶች የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ በጊዜያዊነት በማቋቋም ከአንድ አመት ላነሰ ጊዜ የሚሰሩ ወይም በፔይሮል ክፍያ በማግኘት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው::

14. **“የግል ኢንተርፕራይዝ”** ማለት አንድ የኢንተርፕራይዝ ባለቤት የሚያቋቁመው እና የንግድ ባለቤት ያለው ሆኖ በንግድ ህጉ የሚገኝ አንዱ አደረጃጀት አይነት ሲሆን የአንተርፕራይዙ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና ስራዎች በሙሉ ኢንተርፕራይዙ ባቋቋመው አቅምና ፍላጎት የሚወሰን ነው።

15. **“ህብረት ሽርክና ማህበር”** ማለት ሕጋዊ ሕልውና ያለው ከንግዱ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች ሁሉ ቀላል ቅርጽ ያለው፣ የሸሪኮች አነስተኛ ቁጥር ሁለት ሰው ሲሆን ትልቁ የመስራቾች ቁጥር ገደብ

የሌለው አና የአነስተኛ የመነሻ  ካፒታሉ በውስጠ ደንቡ ውስጥ አባላቱ ዕጣ (ሼር) ድምር በመነሻ ካፒታልነት በመያዝ የሚመሰረት የንግድ ማህበር አይነት ነው፡፡

16. “**ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር**”ማለት በንግድ ህግ አንቀጽ 510 መሠረት ከሁለት አባላት ባላነሰ ከሃምሳ አባላት ባልበለጠ የሚቋቋም ሆኖ የማህበሩ መነሻ ካፒታል ከብር አስራ አምስት ሺ ያላነሰ፣ የማህበሩ አክሲዮን እኩል በሆነ የአክሲዮን ዋጋ የተከፋፈለ ሆኖ የአንድ አክሲዮን ዋጋ ከብር አስር ያላነሰ ሲሆን አባላቱም የተወሰነ ኃላፊነት ያለባቸው ድርጅት/ማህበር ነው፡፡

17. “**የምሥረታ/ጀማሪ ደረጃ**” ማለት ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመመሥረት ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ባሉት የአደረጃጀት አማራጮች ተደራጅተው የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ስራ የሚጀምሩትን ነው::

18. “**የሙያ ብቃት ማረጋገጫ**” ማለት በአንድ የስራ መስክ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት የሚጠየቅ ዝቅተኛ ልምድ /ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ወይንም ሰነድ ነው፡፡

## 3. መርሆዎች

- የሥራ ዕድል ፈጠራው በስራ ፈላጊነት ለተለዩና ለተመዘገቡ ዜጎች ብቻ ነው፣
- የወጣቶች የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣
- የስራ ዕድል ሊፈጥሩየሚችሉ አማራጮችን አሟጦ መጠቀም፣
- ለሥራ ፈላጊዎች ሁሉ አቀፍ ድጋፍ በመስጠት የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፣
- የሚሰጡ ህጋዊነት የማስፈንና መንግስታዊ ድጋፎች በአንድ ማዕከል አገልግሎቶች መስጫ ጣቢያ እንዲያልቁ ማድረግ፣
- ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት፣

## ክፍልሁለት

## 2.1 የስራፈላጊዎችልየታ፣አመዘጋገብእናየግንዛቤፈጠራ

### 2.1.1 ስራፈላጊዎችልየታናምዝገባአስፈላጊነት

ስራ ፈላጊዎችን በጾታ፣ በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ በመመዝገብ እንደ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ዲሞግራፊያዊ ገጽታዎች በመረዳት የፌዴራልና የክልል መንግስታት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ለሚቀርጿቸው የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ዋነኛ ግብዓት ነው። ስለሆነም በልየታና የምዝገባው ስራው ላይ ህብረተሰቡንና አደረጃጀቶችን በማሳተፍ ማከናወኑ በተጨበጭ ስራ ፈላጊ የሆኑ ዜጎችን ለመለየት እና ለስራ ዕድል ፈጠራው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲሁም መንግስት በዘርፉ ለሚያደረገው ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል መሰረት እንዲሆን ማስቻል ነው።

### 2.1.2 የስራ ፈላጊዎች ልየታ

#### 2.1.2.1 የስራፈላጊዎችለመለየትየሚከናወኑተግባራት

**ሀ) የግንዛቤ ስራ ማከናወን**

በሁሉም አካባቢ የሚገኙ ስራ ፈላጊ ዜጎችንና የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በመደበኛው ፕሮግራምና በግዙፍ ፕሮጀክት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተደራጅተው፣ በመንግስት ተቋማት፣ በግል ድርጅቶች በቅጥር የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ለማድረግ በቅድሚያ በስራ ፈላጊነት መመዝገብ ያለባቸው መሆናቸውን በተለያዩ የማስተዋወቂያ እና የግንዛቤ መፍጠሪያ አማራጮች ማለትም በመድረክ፣ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥንና በህትመት ሚዲያ ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ ሀምሌ 1 እና ጥር 1 ጀምሮ ከላይ በተጠቀሱት አማራጮች የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት።

**ለ) መመዝገቢያ ቅፃቅፆችንና መዝገቦችን ማዘጋጀት**

ስራ ፈላጊዎችን ለመመዝገብ ልናዘጋጅ የሚገባን ቅጽ እና የባህር መዝገብ ሲሆን ቅጹ ቤት ለቤት በጊዜያዊነት ስንመዘግብ የምንጠቀምበት ሲሆን የባህር መዝገብ ግን በቋሚነት ስራ ፈላጊዎችን የምንመዘግብበት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚቀመጥ ነው። በጊዜያዊነት ቤት ለቤት ለመመዝገብም ሆነ ዋና የባህር መዝገብ ላይ ከዚህ በታች የተቀመጡ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል።ቀን የስራ ፈላጊው ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ የመኖሪያ አድራሻ (ክልል፣ ከተማ፣ ቀበሌ፣ መንደር፣ የቤት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር)፣የትምህርት ደረጃ፣ ትምህርት የጨረሱበት ዘመን (ዓ.ም)፣ስራ ፈላጊው በዘርፍ ሊሠማሩበት የመረጡት የስራ ዓይነት፣ የተመረጠው

ስራ የሚፈልገው ክህሎት፣ ስራ ፈላጊው ያለበት የክህሎት ክፍተት፣ የሚያስፈልግ የስልጠና ዓይነትና የጊዜ መጠን፣ ኢንተርፕራይዝ ለመመስረት የሚያስፈልግ የአደረጃጀት ዓይነት፣ የስራ ፈላጊነት መታወቂያ ቁጥር፣ የስራ ዕድል ሲፈጠርለት መታወቂያውን የመለሰበት ቀን፣ ስራ ፈላጊው ስራ ሲይዝ ከመዝገቡ ለማቀናነስ የሚያስችል አምዶችን ያካተተ መሆን አለበት። በቅጹ መሰረት የተሰበሰበው የስራ ፈላጊ መረጃን በቋሚነት ለመጠቀም እንዲቻል ከላይ የተዘረዘሩ አምዶች ያሉት የባህር መዝገብ በየክልሉ ቋንቋ ታትሞ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

## ሐ) በስራ ፈላጊነት ለመምዝገብ የሚጠየቁ መስፈርቶች

- የከተማ (የቀበሌ) ነዋሪነት መታወቂያ ያለው/ላት
- የከተማ ነዋሪነት መታወቂያ የሌለው/ላት ከሆነ ቀድሞ ከሚኖርበት/ከምትኖርበት የገጠርም ሆነ የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ማንነቱን/ቷን የሚገልጽ መሸኛ የሚያቀርብ/የምታቀርብ
- እድሜው ከ18 እስከ 60 የሆነ/ነች
- የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ/ነች
- ለመስራት ፍላጎትና ችሎታ ያለው/ላት
- በራሱም ሆነ በቅጥር ቋሚ የገቢ ምንጭ/ቋሚ ስራ የሌለው/ላት

## መ) የምዝገባ ስራውን በንቅናቄ የሚያከናውን ኮሚቴ ማደራጀት

የስራ ፈላጊዎች ምዝገባ በመደበኛነት በዕየለቱ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢዎች ስራ ፈላጊዎች በአካል በመገኘት ከሚያደርጉት ምዝገባ በተጨማሪ በአመት ሁለት ጊዜ በንቅናቄ ቤት ለቤት የሚመዘግብ ኮሚቴ ማደራጀት ያስፈልጋል። ስለሆነም የስራ ፈላጊዎ ልየታና ምዝገባ አስተባባሪ ኮሚቴ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ቀጠና (መንደር) ድረስ መቋቋም የሚኖርበት ሲሆን በተለይ በከተማ፣ በቀበሌና በመንደር (ቀጠና) የሚቋቋም ኮሚቴ አደረጃጃትና ስብጥር የሚከተለውን መያዝ ይኖርታል።

## በከተማ ደረጃ የሚኖር አደረጃጀት፣

1. የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ኃላፊ-----------------ሰብሳቢ
2. የከተማው የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት --------------------------------ም/ሰብሳቢና ፀሀፊ
3. የከተማው የህዝብ አደረጃጀትና ተሳትፎ አማካሪ-------------------------------------አባል
4. የከተማው የሴቶችናየህጻናት ጽ/ቤት ኃላፊ -----------------------------------------አባል
5. የከተማው የወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ---------------------------------------------አባል
6. የከተማው ሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ----------------------------------------------- “
7. የከተማው ወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ ----------------------------------------------- “

8. የከተማው ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ -------------------------------------------- “
9. የከተማው ነዋሪዎች ፎረም ሰብሳቢ ------------------------------------------ “
10. በከተማው ተጨባጭ ሁኔታ መካተት ያለባቸው ሌሎች አደረጃጀቶች ------ “
    ሆነው ይደራጃል ፡፡

## ሠ) ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

- የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስራ የሚመራበትን ዕቅድ በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ማድረግ
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራውን በበላይነት መምራት
- በተዋረድ ያሉት ኮሚቴዎችን ማደራጀት አቅማቸውን መገንባት
- ለምዝገባው ስራ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን የማዘጋጀት
- በከተማው የሚገኙ ስራ ፈላጊዎች በመስፈርቱ መሰረት መለየታቸውን በትክክል በከተማው የሚገኙ ስራ ፈላጊዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ
- በምዝገባው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ መስቀመጥ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ግብረ መልስ መስጠት
- የምዝገባውን አፈጻጸም በተመከለተ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ

## የቀበሌ/ቀጠና የሥራ ፈላጊዎችልየታና ምዝገባ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

1. የቀበሌው አስተዳደር ---------------------------------------------------ሰብሳቢ
2. የቀበሌው የህዝብ አደረጃጀትና ተሳትፎ --------------------------------ም/ሰብሳቢ
3. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አስተባባሪ -----------ፀሃፊ
4. የቀበሌው ወጣቶች ጉዳይ ሃላፊ ----------------------------------------አባል
5. የቀበሌው የሴቶች ጉዳይ ሃላፊ ------------------------------------------ “
6. የቀበሌው የወጣቶች ማህበር ----------------------------------------------“
7. የቀበሌው የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ----------------------------------------“
8. የቀበሌው ነዋሪዎች ፎርም ሰብሳቢ----------------------“
9. በቀበሌው ተጨባጭ ሁኔታ መካተት ያለባቸው ሌሎች አደረጃጀቶች--“ሆነው ይቋቋማሉ፡፡

## ረ) የቀበሌ/ቀጠናየሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ኮሚቴውተግባርናኃላፊነት

- የወረዳውን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ከቀበሌው/ከቀጠናው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ  በማዘጋጀት የጋራ ማድረግ፣
- የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራውን ማከናወን፣
- ቤት ለቤት በመንቀሳቀስ ለስራ ፈላጊዎች እና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መፍጠር፣
- በቀበሌው/ቀጠናው የሚገኙ ስራ ፈላጊዎችን በመስፈርቱ መሰረት መለየት፣
- ለምዝገባው ስራው የሚያገለግሉ ግብዓቶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፣
- በሥራ ፈላጊዎች መመዝገቢያ ቅጹ መሰረት ምዝገባውን ማከናወን፣
- በምዝገባው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ ማስቀመጥ እና ከአቅም በላይ የሆኑትን ለበላይ አካል ማሳወቅ፣
- የምዝገባውን አፈጻጸም ለወረዳው በወቅቱ እና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት ማቅረብ

## 2.1.3 የስራፈላጊዎችአመዘጋገብ

### 2.1.3.1 የከተማነዋሪየሆኑየሥራፈላጊዎችአመዘጋገብ

ማንኛውም የከተማ ነዋሪ በሚኖሩበት አካባቢ በመንደርና ቀጠና ኮሚቴዎች አማካኝነት ወይም በቀጥታ ወደ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በመሄድ ማንነቱን የሚገልጽ የቀበሌ መታወቂያ በመያዝ ምዝገባውን በማከናወን የስራ ፈላጊነት ጊዜያዊ መታወቂያ የሚሰጠው ይሆናል።

### 2.1.3.2 የከተማነዋሪየሆኑናመታወቂያየሌላቸውሥራፈላጊዎችአመዘጋገብ

በየትኛውም ክልል/ከተሞች የሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ/ቴሙትስ ምሩቃን እና ሌሎች የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባን ሲያከናውኑ የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ እና ከቀጠና/ከመንደር አስተባባሪዎች ሥራ የሌላቸው ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ ይመዘገባሉ።

የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸው የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ/ቴሙትስ ምሩቃን እና ሌሎችሥራፈላጊዎችን በቀጠና/በመንደር ኮሚቴዎች እየተረጋገጠ የነዋሪነት መታወቂያ አውጥተው በአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲመዘገቡ ይደረጋል።

### 2.1.3.3 የከተማነዋሪያልሆኑስራፈላጊችአመዘጋገብ፣

ማንኛውምየከተማውነዋሪያልሆኑናበገጠርየሚገኙየዩኒቨርሲቲናየኮሌጅ/የቴሙትስምሩቃንእናሌሎችሥራፈላጊወገኖችቀድሞይኖሩበትከነበረውየገጠርምሆነየከተማቀበሌአስተዳደርስለማንነታቸውየሚገልጽመሸኛደ

ብዳቤይዘው፣መስራትበሚፈልጉበትከተማውስጥበሚገኝየአንድማዕከልአገልግሎትመስጫጣቢያይመዘገባ ሉ።በመሸኛውመካተትያለባቸውዋናዋናመረጃዎች፣-

- ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ የት/ደረጃ ፣ የሰለጠነበት ሙያ፣ የሥራ ልምድ ወይም ዝንባሌ፣
- ቀደም ሲል ይኖርበት ከነበረው ክልል፣ ከተማ፣ ቀበሌ ቋሚ ሥራ የሌለው መሆኑና በነበረበት ቦታ ምን ሲሰራ እንደነበረ፣
- በነበረበት ቦታ ከማንኛውም ወንጀል ነጻ መሆኑን እና የመንግሥትም ሆነ የግል ዕዳ ወይም ብድር የሌለበት መሆኑን፣
- አካባቢውን ለመልቀቅ የፈለገበት ምክንያት የሚገልጽ እና በመሸኛው ላይ ሥድስት ወር ያላለፈው ፎቶግራፍ ኖሮት ማህተም የተደረገበት፣ የመሸኛ ደብዳቤ አቅርቦ ጊዜያዊ የሥራ ፈላጊነት መታወቂያ ይሰጠዋል።
- ይህ መታወቂያ የሚያገለግለው ለአንድ የምዝገባ አመት ማለትም ለአንድ አመት ብቻ ይሆናል።

## 4.4 የስራፈላጊዎችመመዝገቢያወቅት

የምሩቃንና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች ምዝገባ የሚከናወነው በአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በዘርፉ የስራ ፈላጊዎች መመዝገቢያ መዝገብ መሠረት ይሆናል። ምዝገባው በዓመት ሁለት ጊዜ ከሐምሌ እሰከ ነሐሴ እና ከጥር እስከ የካቲት ወር በየደረጃው በተዋቀረው ኮሚቴዎች አማካይነት በአጠቃላይ በንቅናቄ ቤት ለቤት ቅስቀሳ በማካሄድ ይከናወናል። በተጨማሪም በማንኛውም የስራ ሰዓት የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የስራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስራ በመደበኛነት ያከናውናሉ።

## 4.6 የስራፈላጊዎች ምዝገባአፈጻጸምሪፖርት አቀራረብ

በሁሉምክልሎችናየከተማአስተዳደሮች በሚገኙ የአንድማዕከልአገልግሎትመስጫጣቢያዎችየተሟላየሥራፈላጊዎችመረጃበማደራጀትናከተመዘገቡየዩኒቨር ስቲናኮሌጅምሩቃን እና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች በትምህርት ደረጃ፣ በፆታ፣ በዕድሜ በመለየት በተዘጋጀው የስራ ፈላጊዎች መመዝገቢያ ባህር መዝገብ ላይ መስፈር አለበት። በየስራ ፈላጊዎች ምዝገባ አፈጻጸም ሪፖርት ለማድረግ የተዘጋጀውን ቅጽ 001 በመጠቀም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለከተማ በየሳምንቱ ፣ለከተማ/ለክልል በየ15 ቀኑ እና ከክልል ወደ ፌደራል በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

## 4.7 የስራፈላጊዎችየግንዛቤፈጠራ

የስራ ፈጣሪነት አመለካከት፣ ክህሎት እና የንግድ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት ስልጠና አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠና ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙት የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀሲዎች /መምሪያዎች /ጽ/ቤቶች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በስራ ፈላጊነት ለተመዘገቡ ዜጎች በዘርፉ ያሉትን አማራጮች እና ከስራ ፈላጊው ስለሚጠበቅ ዝግጁነት የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀት የስራ ፈላጊ ወላጆችን ጨምሮ የተለያዩ የህብረተሰብ አካላት በስራ ዕድል ፈጠራ ስራ ያላቸውን ሚና በማስገንዘብ የጠራ አመለካከት ይዘው እንዲሄዱ የሚደረግ ይሆናል። ለስራ ፈላጊዎች የተፈጠረ የግንዛቤ ፈጠራ አፈጻጸም ሪፖርት ለማድረግ የተዘጋጀውን ቅጽ 002 በመጠቀም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎች ለከተማ በየሳምንቱ፣ከከተማ ለክልል በየ15 ቀኑ እና ከክልል ለፌደራል በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

## 4.8 የስራፈላጊዎችየአጫጭርየስራአመራርእናክህሎትስልጠና

በየደረጃው ከሚገኙ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለስራ ብቁ ሊያደርጋቸው የሚችሉ አጫጭር የንግድ ስራ አመራር (መሰረታዊ የስራ ፈጣሪነት አመለካከት፣ በአደረጃጀት አማራጮች፣ የንግድ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት፣ መሰረታዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ የወጪ ማስላትና ዋጋ ተመን፣ ንብረት አያያዝ፣ ደንበኛ አያያዝ) እና የቴክኒክ ስልጠና አይነቶችን በመለየት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ከተመዘገቡ ከስራ ፈላጊዎች ዘርፍ ምርጫ ጋር በማጣጣም የሚያመቻች ይሆናል ።ለአዲስ ስራ ፈላዎችና አንቀሳቃሾች ገበያ ተኮር አጫጭር የስራ አመራር እና የክህሎት ስልጠና በመስጠት እንዲመዘኑና በሙያ ብቃት ማረጋገጫነት የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ የሚያገለግል ይሆናል። ለስራ ፈላጊዎች የተሰጠ አጫጭር ንግድ ስራ አመራር እና ክህሎት ስልጠና አፈጻጸም ሪፖርት ለማድረግ የተዘጋጀውን ቅጽ 003 በመጠቀም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎች ለከተማ በየሳምንቱ፣ከከተማ ለክልል በየ15 ቀኑ እና ከክልል ለፌደራል በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

## ክፍልሶስት

# 5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችአደረጃጀትእናየስራዕድልፈጠራአማራጮች

## 5.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችአደረጃጀትአማራጮች

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ለመሰማራት የሚፈልጉ ስራ ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተለያዩ የአደረጃጀት አማራጮች መዝግቦ ወደ ሥራ ለማስገባት በተገልጋዮች ፍላጎት መነሻነት በሀገራችን የንግድ ሕግ እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ መሠረት በማድረግ አገልግሎቱ ይሰጣል።

### 5.1.1የአደረጃጀትዓይነቶች

ሀ) በግል የሚቋቋም ኢንተርፕራይዝ፤

ለ) በንግድ ሕግ መሰረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር፤

#### 5.1.1.1 በግልየሚቋቋምኢንተርፕራይዝመስፈርት

የግል ኢንተርፕራይዝ  አንዱ የአደረጃጀት አይነት ሲሆን የኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና ስራዎች በሙሉ ኢንተርፕራይዙ ባቋቋመው አቅምና ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፡፡ መስፍርቶቹም ፡-

1. የስራ ዕጥ መታወቂያ ካርድ
2. የአመልካቹበስድስትወርጊዜውስጥየተነሳውጉርድፎቶግራፍ፣
3. የነዋሪነት የመታወቂያካርድኮፒ፣
4. ዕድሜው18 ዓመትየሞላውመሆን፣
5. ለንግድሥራየሚጠቀምበትአድራሻያለው መሆን፣
6. የመነሻ ካፒታል ማስረጃ
7. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት
8. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

#### 5.1.1.2 የንግድማህበርአደረጃጀትዓይነቶችናመሥፈርት

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጥቃቅንናአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመሰረቱባቸው በኀብረት ሽርክና ማኀበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበርና አልፎ አልፎ የሕብረት ሥራ ማኀበራት ሲሆኑ የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀትም በአብዛኛው በእነዚህላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

#### 5.1.1.3 በኀብረትሽርክናማኀበርአደረጃጀትናመስፈርት

የኀብረት ሽርክና ማህበር አደረጃጀት ሕጋዊ  ሕልውና ያለው ከንግዱ ማኀበራት ወይም ድርጅቶች ሁሉ ቀላል ቅርጽ ያለው አደረጃጀት ነው፡፡ በህብረት ሽርክና አደረጃጀት የሽሪኮች አነስተኛ ቁጥር ሁለት ብቻ ሲሆን የአነስተኛ ካፒታል ጥያቄ ገደብ የለበትም፡፡ ካፒታሉ በውስጠ ደንቡ ውስጥ ቢካተትም ከምዝገባ በፊት መክፈሉ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የሙያ ወይም የአገልግሎት መዋጮ የተፈቀደ ነው፡፡ የማቋቋሚያ**መስፈርቱም ፡-**

1. የስራ ዕጥ መታወቂያ ካርድ
2. በሁሉምመስራችአባላትየተፈረመማመልከቻማቅረብ፣
3. የአባላቱ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ኮፒ ማቅረብ
4. የፀደቀየንግድስምስያሜማስረጃ

5. የግብርከፋይነትመለያቁጥርማስረጃ
6. የአዋጭነትየንግድስራእቅድማቅረብ
7. ከአንድማዕከልአገልግሎትመስጫ ጣቢያየማኅበሩየመመስረቻጽሑፍእናየመተዳደሪያደንብናሙናበመውሰድየማኅበሩንየመመስረቻጽሑፍእናየመተዳደሪያደንብበአባላትአጸድቆማቅረብ፣
8. የመስሪያቦታቋሚአድራሻ
9. ስራ ለመጀመር የሚያስችል መነሻ ካፒታል
10. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### 5.1.1.4 ኃላፊነቱየተወሰነየግልማኅበር

ኃላፊነቱ የተውሰነ የግል ማኅበር በንግድ ከሁለት አባላት ባላነሰ ከሃምሳ አባላት ባልበለጠ የሚቋቋም ሆኖ የማህበሩ መነሻ ካፒታል ከብር አስራ አምስት ሺ ያላነሰ፣ የማህበሩ አክሲዮን እኩል በሆነ የአክሲዮን ዋጋ የተከፋፈለ ሆኖ የአንድ አክሲዮን ዋጋ ከብር አስር ያላነሰ ሲሆን አባላቱም የተውሰነ ኃላፊነት ያለባቸው ድርጅት/ማህበር ነው። የማቋቋሚያ**መስፈርቱም ፡-**

1. የስራ ዕጥ መታወቂያ ካርድ
2. የአመልካቾቹ የከተማ ነዋሪነት መታወቂያ ፎቶኮፒ ማቅረብ፣
3. በሁሉም አባል የተፈረመ ማመልከቻ
4. የፀደቀ የንግድ ስም ስያሜ ማስረጃ
5. የመመሥረቻ ጽሑፉንና መተዳደሪያ ደንብ በአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያ በማቅረብ ያጸድቃሉ፣
6. ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅቶ ማቅረብ
7. 15 ሺ ብር በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም አስገብቶ ማስረጃ ማቅረብ
8. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት
9. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማውጣት
10. የመስሪያቦታቋሚአድራሻ

### 5.1.2 የህጋዊ ሰውነት ሰርተፍኬት አሰጣጥ

በግልም ሆነ በማህበር በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ወደ ስራ ለሚገቡ ኢንተርፕራይዞች ለመደራጀት የሚያስፈልጉ ተብለው የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልተው የመመስረቻ ጽሁፍና

መተዳደሪያ ደንባቸውን ካፀደቁ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ መሆናቸውን የሚገልጽ የህጋዊነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ወደ ስራ የሚገቡ ስራ ፈላጊዎች አደረጃጀታቸውን እንደጨረሱ በጀማሪ ደረጃ የሚሰጣቸው ሰርተፍኬት ይሰጣቸዋል፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ መደራጀታቸውን የሚገልጽ ሰርተፍኬት ከተሰጣቸው በኋላ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እንዲያወጡ ይደረጋል፡፡

### 5.1.3የተደራጁኢንተርፕራይዞችሪፖርትአደራረግ

በስራ ፈላጊ ባህር መዝገብከተመዘገበበኋላስራፈላጊዎቹወደስራ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችበተደራጁበት ዋና የስራ ዘርፍ፣አጠቃላይ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ብዛትና የአባላትብዛት፤በፆታ ተለይቶ፣ እንዲሁም ከአጠቃላዩ በወጣቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ብዛትና ወጣት አባላት ብዛት በተዘጋጀውሪፖርትማቅረቢያቅጽ 004 መሰረትሪፖርትመደረግይኖርበታል፡፡

## 5.2 የስራዕድልፈጠራመንገዶች

### 5.2.1 በመደራጀትየሚፈጠርየስራዕድል

ስራ ፈላጊዎችን ከምዝገባ ጀምሮ የተለያዩ መንግስዊ ድጋፎችን በማመቻቸት በመረጡት የአደረጃጀት አይነቶች ተደራጅተው በሚሰጣቸው የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና በሚያወጡት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ መሰረት ወደ ስራ በሚገቡ መሰረት ወደ ስራ በሚገቡ አዲስ የሚፈጠር ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል ነው፡፡ በአደረጃጀት የሚፈጠር የስራ ዕድል የራስ ስራ ፈጠራ ወይም (self employment) የሚባል ሲሆን የተፈጠረውን የስራ ዕድል ሪፖርት በቅጽ 005 መሰረት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

### 5.2.2 በቅጥርየሚፈጠርየስራዕድል

ስራፈላጊዎችበቂስልጠናወስደውየብቃትማረጋገጫሰርተፍኬትካገኙበኋላተደራጅተውየራሳቸውንኢንተርፕራይዝ በማቋቋምየስራዕድልመፍጠር ላልቻሉ ስራ ፈላጊዎች በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣መንግስታዊ ያልሆኑተቋማት፣ በነባር ኢንተርፕራይዞች፣ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣በግዙፍ የመንግስት ፕሮጀክቶች፣በሆቴሎችና በተለዩ የግል ኢንቨስትመንቶች ላይ በቋሚና በጊዜያዊ ቅጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል ነው፡፡ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በአካባቢያቸው በቅጥር የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉመንግስታዊና መንገስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በመለየት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት ለስራ ፈላጊ ዜጎች በቅጥር የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ መስራት ይጠበቃል፡፡ በመንግስት መዋቅር በዜሮ አመት ለምሩቃን በቅጥር የሚፈጠር የስራ

እድል በቋሚነት ተይዞ በስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ሪፖርት መቅረብ ያለበት ሲሆን አጠቃላይ በቅጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል በአባሪ በተቀመጠው ቅጽ 005 መሰረት ሪፖርቱ ተሞልቶ ለሚመለከተው አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 5.3 የስራዕድልፈጠራሪፖርትአደራረግጥንቃቄማድረግየሚገቡጉዳዮች

1. አደረጃጀታቸውን ጨርሰው ወደ ስራ ያልገቡ ስራ ፈላጊዎች አደረጃጀታቸውን ብቻ ስለጨረሱ ብቻ የስረ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል ተብሎ መያዝም ሆነ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ የለበትም፡፡ አደረጃጀታቸውን ጨርሰው ነገር ግን ወደ ስራ ያልገቡ አደረጃጀት የጨረሱና የስራ ዕድል ያልተፈጠረላቸው ተብሎ ተይዞ የስራ ዕድል ለመፍጠር ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡
2. በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ስራ የገቡ በአጠቃላይ ቋሚ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ተብሎ ሪፖርት መደረግ ያለበት ሲሆን በጥሪት ማፍሪያ አማራጮች ላይ ተደራጅተው ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰሩ ወደ ስራ የተሰማሩት ተለይተው በጊዜያዊ የስራ ዕድል ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡
3. ከጥሪት ማፍሪያ ከተሰማሩት ውጪ በቅጥር በጊዜያዊነት የሚፈጠረውን የስራ ዕድል በተደጋጋሚ የመቁጠር ችግር ለመቅረፍ እንዲያስችል ሰዎች በወራት በሚል አሰራር መሰረት በስራ ዕድል ፈጠራና ሌሎች የዘርፉ ሪፖርቶችና መረጃዎች አሰባሰብ፣አደረጃጀትና አያያዝ ማንዋል ላይ በተቀመጠው አግባብ ተዘጋጀቶ ሪፖርቱ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍልአራት

## 2. የባለድርሻአካላትሚና

### 1. በየደረጃው የሚገኙ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ም/ቤት ተግባርና ሀላፊነት፣

የምክር ቤቱ አባላት የሆኑ መንግሥታዊ አካላት ለሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ እስከ የስራ ዕድል ፈጠራ ሰራ በቀጥታ በመሳተፍ በጋራ ይሰራሉ፣

1. በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት አባል መ/ቤት ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣
2. በሥራ ፈላጊነት ከተመዘገቡት ውስጥ የሥራ ዕድል የተፈጠረለት ኃይል ተለይተው መታወቁን ያረጋግጣል፣
3. የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ግልጽ፣ ጥራት ያለውና አስፈላጊውን መረጃ ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. ሥራ ፈላጊዎች በወቅቱ መመዝገባቸውን፣ የተሟላ ኦሬንቴሽን ማግኘታቸውንና በየደረጃው የተሟላ መረጃ መደራጀቱን ያረጋግጣል፣
5. የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ፣አቅጣጫ ያስቀምጣል

### 2. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተግባርና ሀላፊነት፣

1. የስራ ዕድል ፈጠራ የሚረዱና የሚሻሻሉ ህጎች ማጥናትና ለመንግስት ማቅረብ ሲፈቀድም ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ
2. የስራ ፈላጊዎች ምዝገባ፣ከግንዛቤ ፈጠራ፣አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ተግባራትን ከተሞች እንዲደግፉእና በበላይነት እንዲፈጽሙ በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል
3. በስራ ፈላጊዎች ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በየደረጃው እንዲሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
4. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድልመፍጠሪያ አማራጮች ለክልልና ከተማ አስተዳደሮች የአቅም ግንባታ ስራዎች ያከናውናል
5. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸሞችን በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ እና በስድስት ወር ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል

## 3. የፌዴራልየከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

1. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድል ፈጠራ የሚመራበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ይደግፋል፣
2. የዘርፉን የክልል /የከተማ አስተዳደሮችን አቅም ይገነባል ፣
3. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድል ፈጠራ በተቀመጠው መሰረት እንዲፈጸም ይደግፋል፣ ይከታተላል ያስተባብራል፣
4. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ ችግሮችን ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችል ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ያከናውናል መድረኮችን በመፍጠር በውይይት እንዲዳብሩ እና እንዲጎለብቱ ያደርጋል
5. በስራ ፈላጊዎች አመዘጋጋብ፣አደረጃጀትና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ለዘርፉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስገመግማል፣ የተደረሰበትን የጋራ ስምምነት አፈፃፀም ይከታተላል፣
6. በስራ ፈላጊዎች ምዝገባ፣ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች እና የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች መረጃዎችን በዳታ ቤዝ እንዲደራጅ ለማድረግ የሚስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል ፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል ይደግፋል፣
7. በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክት የስራ ዕድል ፈጠራ የጋራ ዕቅድ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ተወካይ ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለአስፈፃሚ አካላት ያሳውቃል፣
8. ሥራ ፈላጊዎች ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አካባቢ ከሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተመልምለው በፕሮጀክቶቹ የስራ ዕድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣
9. በመንግስት ፕሮጀክቱ የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች መረጃ ማሰባሰቢያ ቅፅ በማዘጋጀትና በፌደራል ደረጃ ፕሮጀክቱን ከሚከታተለው ተቋም እና ለክልሎች ያሰራጫል፣
10. በስራ ዕድል ፈጠራው ላይ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመለየት በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈቱ ያደርጋል፣
11. ስራ ፈላጊዎቹ በየስራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣
12. የቁጠባ ባህል ለማዳበር ከሚያገኙት ገቢ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎቹ የሚቆጥቡበትን አሰራር በመዘርጋት፣ በዚህ ዘርፍ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ ቋሚ ኢንተርፕራይዝ ለመሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል መደረጉን ያረጋግጣል፣

**4. በየደረጃው ያሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ/ጽ/ቤት፣**

1. ለተመዘገቡ ስራ ፈላጊዎች ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ከአሰሪዎች ጋር የማገናኘት ስራ ያከናውናል
2. በሀገር አቀፍ ደረጃና በየክልሉ/ከተማው የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስርዓት ተጠናክሮ በጥራት እንዲከናወን እና ለዘርፉ ልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲውልበቅንጅት ይሰራል፣

**5. በየደረጃው ያሉየሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ/ጽ/ቤት፣**

1. ስራ ፈላጊ ሴቶችን በመለየት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ እንዲመዘገቡ ግንዛቤ በመፍጠር አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፣
2. የተመዘገቡት ሥራ ፈላጊ ሴቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ከዘርፉ አስፈፃሚዎች ጋር የጋራ ዕቀድ ያዘጋጃል ይተገብራል፣
3. በሀገር አቀፍ ደረጃና በየክልሉ/ከተማው የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስርዓት ተጠናክሮ በጥራት እንዲከናወን እና ለዘርፉ ልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲውልበቅንጅት ይሰራል፣
4. ለስራ ፈላጊ ሴቶች ምዝገባ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ የሴቶች አደረጃጀቶችን (ሊግ፣ ማህበር፣ ፎርምና ፌደሬሽን) አቅም በመገንባትና ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣
5. በሴቶች የተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ የመከታተልና የማበረታታት ስራ ያከናውናል፣
6. በስራ ፈላጊዎች ምዝገባ፣አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በመስክ ክትትል ድጋፍና በመድረግ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

**6. በየደረጃው ያሉወጣቶችና ስፖርት ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርናሀላፊነት፣**

1. ስራ ፈላጊ ወጣቶችን በመለየት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ እንዲመዘገቡ ግንዛቤ መፍጠር አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፣
2. የተመዘገቡት ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ከዘርፉ አስፈፃሚዎች ጋር የጋራ ዕቀድ ያዘጋጃል ይተገብራል፣
3. በሀገር አቀፍ ደረጃና በየክልሉ/ከተማው የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስርዓት ተጠናክሮ በጥራት እንዲከናወን እና ለዘርፉ ልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲውልበቅንጅት ይሰራል፣
4. ሥራ ፈላጊ ወጣቶችንምዝገባ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ የወጣት አደረጃጀቶችን (ሊግ፣ ማህበር፣ ፎርምና ፌደሬሽን) አቅም መገንባትና ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣
5. በወጣቶችየተቋቋሙ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ የመከታተልና የማበረታታት ስራ ያከናውናል፣

6. በስራ ፈላጊዎች ምዝገባ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በመስክ ክትትል ድጋፍና በመድረግ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

## 7. የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

1. በየደረጃው ካሉት የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በየአመቱ ያለውን የሥራ ፈላጊዎች የተሟላ ፕሮፋይልና መረጃ አሰባሰብ ስርዓት ይነድፋል፣አቅም ይገነባል፣
2. በሀገሪቱ ባሉት ከተሞች የሥራ አጥ ብዛት እና በዘርፉ የስራ እድል የተፈጠረላቸውን በማነጻጸር መረጃዎች እንዲያዝና ለዘርፉ ልማት ስራ በግብአትነት እንዲውል ያደርጋል፣
3. በዘርፉ ልማትም ሆነ በሌሎች የልማት ዘርፎች የተፈጠረ የሥራ ዕድል፣ መረጃ በመሰብሰብ የኢንተርፕራይዞች ልማት ለስራ እድል ፈጠራ ያለውን ሚና የሚያሳይ መረጃ" ያደራጃል፣
4. በሀገሪቱ የሥራ አጥነት ቁጥር በምን ደረጃ እየቀነሰ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ አሰባሰብና አዘገጃጀት ላይ በጋራ ይሰራል::

## 8. በየደረጃው የሚገኙ የንግድ ቢሮዎች ተግባርና ሀላፊነት፣

1. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ገብቶ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ይመድባል፣
2. በንግድ ህጉ እና የአሰራር መመሪያዎች ላይ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ይሰራል፣
3. አዲስ ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች የተቀላጠፈ የንግድ ስም ምዝገባ፣ የዋና ምዝገባ እና የንግድ ፍቃድ ምዝገባ አገልግሎት በመስጠት ይሰጣል፣
4. የኢንተርፕራይዞችን የህጋዊ ሰውነት ሰነድ የማደስ አገልግሎት ይሰጣል፣
5. ህጋዊ አሰራር ያልተከተሉ ኢንተርፕራይዞች ህጋዊ ሰውነታቸው እንዲሰረዝ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፣

## 9. የገቢዎችና ጉምሩክ ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርናሀላፊነት፣

1. በአዲስ ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ይሰጣል፣
2. በገቢ አስተዳደር ስርዓት ዙሪያ ለኢንተርፕራይዞች ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ይሰራል፣
3. የገቢ ክሊራንስ ለሚጠይቁ ኢንተርፕራይዞች መረጃ ይሰጣል፣

## 10. በየደረጃው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተግባርናሀላፊነት፣

1. በስራ ፈላጊነት ለተመዘገቡ ዜጎች ወደ ስራ ሊያስገባ የሚችል አጫጭር የአመለካከትና የክህሎት ስልጠና ይሰጣል፣
2. የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠናተቋም ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ጋር በመቀናጀት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጣቸውን የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ የሚገኙ አነስተኛ ኢንተርፕራይቾ በመለየት አገልግሎት ይሰጣል።
3. በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ለሚገኙ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ ስርዓት ዝርጋታ አገልግሎት ይሰጣል።
4. ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አመቻች ኦፊሰር ጋር በመቀናጀት ለኢንተርፕራይዞቹ የተሰጡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መረጃዎች ያደራጃል ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል።
5. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በጋራ ዕቅድ መሰረት መፈጸሙን ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ጋር በመሆን ይገመግማል የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም ያስቀምጣል፤

## 11. የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የሚያስባብሩ አካላት ተግባርና ሀላፊነት፣

1. ከፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስት ኤጀንሲ ጋር በመሆን የጋራ ዕቅድ አዘጋጅቶ መፈራረም፤
2. የመንግሥት ፕሮጀክቶች ባሉባቸው ክልሎች በሚገኙ የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የግዙፍ ፕሮጀክቶች ተወካይ እንዲኖር ማድረግ፣
3. ስራ ፈላጊዎች ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አካባቢ ከሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተመልምለው በፕሮጀክቶቹ የስራ ዕድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በየፕሮጀክቱ የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች መረጃ ማሰባሰቢያ ለሚመለከተው አካል ማሰራጨት፣
5. በስራ ዕድል ፈጠራው ላይ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመለየት መፍታት፣
6. ስራ ፈላጊዎቹ በየስራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፣
7. የቁጠባ ባህል ለማዳበር የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎቹ የሚቆጥቡበትን አሰራር በመዘርጋት፣ በዚህ ዘርፍ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ ቋሚ ኢንተርፕራይዝ ለመሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

8. በየክልሎች በሚገኙ ፕሮጀክት ሳይቶች የተፈጠረውን የስራ ዕድል መረጃ በዕድሜ በፆታና በትምህርት ደረጃ ለይቶ እንዲሰባሰብ በማድረግ ለፌደራል የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወቅቱን ጠብቆ ሪፖርት ማድረግ፣

## 12. የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም

1. የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራብ ተቋማት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ገብቶ የሚሰራ ባለሙያ ይመድባል፣
2. ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልግ የፋይናንስ አቅርቦትንያመቻቻል፡
3. የብድር ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችል የቁጠባ አሰባሰብ ሥርዓት እንዲኖረው የተለያዩ አሠራሮችን በመዘርጋት ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡
4. ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ አቅርቦት ቀልጣፋ በሆነ መልኩና በወጣው የአገልግሎት ስታንዳርድ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. ለጥቃቅንኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅርቦትን ለማረጋገጥ በቅድመ ብድርና ድህረ ብድር የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየትና በዕቅድ ውስጥ በማካተት ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡
6. በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ተመድበው የሚሰሩ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም ባለሙያዎችን አቅም በየጊዜው ይገነባል፡፡

## 13. የክልል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

1. በተዘጋጁት ቅጾች መሠረት መረጃዎችን ከዞን የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ያሰባስባል፣
2. የመረጃዎቹን ጥራት በመስክ ጉብኝት ያረጋግጣል፣ የተሰበሰበውን መረጃ ጥራት ገምግሞ ወደ ዳታ ቤዝ ያስገባል፣
3. በማንዋሉ ላይ በተጠቀሱት የሪፖርት ማድረጊያ ጊዜያት መሠረት ለፌዴራል የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ይልካል፣
4. መረጃዎቹን መሠረት በማድረግ ለፖሊሲ ውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን በስታቲስቲክ መጽሄት፣ ዳይሬክተሪና በተለያዩ ዘዴዎች በማጠናቀር ለመረጃ ፈላጊዎች ወይም ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣

5. በመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ዙሪያ ለመረጃ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፣
6. ስራ ፈላጊዎችን የኢንዱስትረ ፓርክ በሚገኝበት አካባቢ ካሉ ዞኖች እና አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫጣቢያዎችን በማስተባበር የስራ ፈላጊዎች ምልመላ እንዲካሄድ በማድረግ የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣
7. በየኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል መረጃ በፆታና በትምህርት ደረጃ ለይቶ እንዲሰባሰብ በማድረግ ለፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ያስተላልፋል፣
8. የፕሮጀክቶቹ አንቀሳቃሾች የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ሃላፊነት እየተወጡ መሆናቸውን መከታተል፣
9. የዘርፉ አስፈፃሚ አካላት ማለትም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎችና ተቋማት፣ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራብ ተቋማት ዕቅዱ በተሟላ ሁኔታ እንዲፈፀም የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ሃላፊነት እንዲወጡ ያስተባብራል፣
10. የቁጠባ ባህል በማዳበር አንቀሳቃሾች ከገቢያቸው እንዲቆጥቡ በማድረግ በዚህ ዘርፍ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ ቋሚ ኢንተርፕራይዝ መሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

## 14. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ

1. የስራ ፈላጊዎች ምዝገባ፣ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች እና የሥራ ዕድል ፈጠራ መረጃዎቹን በተዘጋጁት ቅጾች መሠረት በጥራት ያስባስባል፣
2. በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ከአደረጃጀቶች ጋር በመሆን ምዝገባ ያከናውናል፣
3. የተሰበሰበውን መረጃ ወደ ዳታ ቤዝ ያስገባል፣
4. ከባለድርሻ አካት ጋር በመሆን ለሥራ ፈላጊዎች የህጋዊነት ማስፈንና አደረጃጀት ድጋፍ ይፈጽማል፣ አፈፃፀሙን ለሚመለከታቸው አካላት በማዘጋጀት ያሰራጫል፣
5. የዘርፉ መረጃ በጥራት እንዲያዝ የሚመለከተውን ባለሙያ አቅም ይገነባል፣
6. በማኑዋሉ ላይ በተጠቀሱት የሪፖርት ማድረጊያ ጊዜያት መሠረት መረጃዎችን ለወረዳው/ከተማው የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ይልካል፣

## 15. የከተማ /ወረዳ/ ቀበሌ አስተዳደር፣

1. በከተማው /ወረዳው/ ቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሥራ ፈላጊ ወገኖች በአንድ ማዕከል አገልግሎት ቀርበው እንዲመዘገቡ አስፈላጊውን የቅስቀሳ፣ የግንዛቤ ፈጠራና የማነሳሳት ሥራ ያከናውናል፣
2. ከቀበሌ በታች ባለው የቀጠና /የመንደር ኮሚቴዎች/ አስተባባሪዎች አማካኝነት ሥራ ፈላጊ ወገኖች በሙሉ መመዝገባቸውን ቤት ለቤት በመዘዋወር ያረጋግጣሉ፣ ያልተመዘገቡ ካሉ እንዲመዘገቡ ክትትል በማድረግ መረጃውን ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ይሰጣል:: በሥራ ዕድል ፈጠራው ሁሉንም ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረገው ሥራ ተሳታፊ ይሆናል፣
3. የነዋሪነት መታወቂያ ለሌላቸው ሥራ ፈላጊ ወገኖች ከነበሩበት ከተማ/ቀበሌ መሸኛ እንዲያመጡ በማድረግ፣ መታወቂያ በመስጠት፣ እንዲመዘገቡና በሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል::
4. የሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ስርዓት በከተማው /በወረዳው/ ቀበሌው በተፈለገው ጥራትና መረጃው በሚፈለግበት ጊዜ ተመዝግቦ ለሚመለከተው አካል መተላለፉን ያረጋግጣል፣ መረጃው ለዘርፉ ልማት ዕቅድ ዝግጅት እንዲውል ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል::
5. በተዘጋጁት ቅጾች መሠረት መረጃዎችን ከአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ያሰባስባል፣
6. የተሰበሰበውን መረጃ ጥራት ገምግሞ ወደ ዳታ ቤዝ ያስገባል፣
7. የመረጃዎቹን ጥራት በመስክ ጉብኝት ያረጋግጣል፣
8. የመረጃ ጥራት እንዲጠበቅየባለሙያ እና የአመራር አቅም እንዲጠናከር ያደርጋል፣
9. በማኑዋሉ ላይ በተጠቀሱት የሪፖርት ማድረጊያ ጊዜያት መሠረት ለዞን የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ይልካል፣
10. በመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ዙሪያ ለመረጃ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፣

## ክፍልአምስት

## 3. የድጋፍ ክትትል እና ግብረ መልስ አግባብ

### 7.1 ሪፖርት

የክልሎች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየደረጀው ከሚገኙ የዘርፉ መዋቅር የሚያሰባስቡበትና የሚያዘጋጁበት የጊዜ ገደብ እንዳለ ሆኖ የዘርፉን ሪፖርት አቀራረብ ወቅቱን የጠበቀ ከማድረግ አንጻር እንደሚከተለው እንዲቀርብ መደረግ አለበት።

### 7.1.1 የወርሃዊሪፖርትአቀራረብ፣

1. አንድ ማዕከል አግልገሎት መስጫ ጣቢያዎች ለከተማ/ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ወር በገባ እስከ 23ኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
2. የከተማ /ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለዞንየስራ ዕድልና ምግብ ዋስትና ጽቤት ወር በገባ እስከ 25ኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
3. የዞንየስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለክልል ኤጄንሲ/ቢሮ ወር በገባ እስከ 27ኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
4. ክልሎች ወርሃዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን ወር በገባ እስከ 30ኛው ቀን ድረስ ለፌዴራል ኤጄንሲው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
5. የኤጄንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በቀጣዩ ወር እስከሶስተኛው ቀን ድረስ የወሩን ሪፖርት አጠቃሎ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀርባል።

### 7.1.2 የሩብዓመትዕቅድክንውንሪፖርትአቀራረብ፣

1. የአንድ ማዕከል አግልገሎት መስጫ ጣቢያዎች ለከተማ/ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የየሩብ ዓመት ሪፖርት በሩብ ዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 23ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
2. የከተማ /ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለዞን የስራ ዕድልና ምግብ ዋስትና ጽቤት የየሩብ ዓመት ሪፖርት በሩብ ዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 25ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
3. የዞን የስራ ዕድልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለክልል ኤጄንሲ /ቢሮ የየሩብ ዓመት ሪፖርት በሩብ ዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 27ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

4. ክልሎች የዞርፉን የተጠቃለለ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 30ኛው ቀን ድረስ ለኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፣
5. የኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬትየተጠቃለለ የየሩብ ዓመት ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቀጣዩ ወር በገባ እስከ ሶስተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፣

### 7.1.3 ዓመታዊየዕቅድክንውንሪፖርትአቀራረብ

1. የአንድ ማዕከል አግልገሎት መስጫ ጣቢያዎች ለከተማ/ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የዓመቱን ሪፖርት በዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 23ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
2. የከተማ /ወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለዞንየስራ ዕድልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች የዓመቱን ሪፖርት በዓመቱ መጨረሻ ወር እስከ 25ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
3. የዞን የስራ ዕድልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች ለክልል ኤጀንሲ/ቢሮ የዓመቱን ሪፖርት በዓመቱ የመጨረሻ ወር እስከ 27ተኛው ቀን ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
4. ክልሎች የዞርፉን የተጠቃለለ ሪፖርት በዓመቱ የመጨረሻ ወር እስከ 30ኛው ቀን ድረስ ለኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፣
5. የኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የተጠቃለ የዓመቱን ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እስከ ሐምሌ 3 ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፣

### 7.2 የአካል

1. በመዋቅሩ ካሉ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በየሩብ ዓመቱ በኤጀንሲው መድረክ በማዘጋጀት በጋራ የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ለቀጣይ ስራዎችና ለታዩ ክፍተቶች መፍትሄ ማስቀመጥ፣
2. ከዘርፉ አስፈጻሚ አካላትና ከህዝብ ክንፍ አደረጃጀቶች ጋር የዕቅድ አፈጻጸሙን በጋራ በመገምገም ለቀጣይ ስራዎችና ለታዩ ክፍተቶች መፍትሄ ማስቀመጥ፣

### 7.3 የመስክላይክትትል

የፌዴራል ኤጀንሲው፣ ክልሎች እና በየደረጃው የሚገኙ መዋቅሮች በዕቅድ አፈጻጸማቸው ወቅት የሚያጋጥማቸውን ክፍተቶችን ለመሙላትና የተሻሉ አፈጻጸሞችን የበለጠ ለማጠናከርና ወደ ሌሎች ለማስፋት የመስክ ክትትልና ድጋፍ ስራ በመስራት የመስክ ሪፖርቱን ለሚመለከተው

አካል በወቅቱ ማቅረብና ግብረ-መልስ መስጠት የክትትልና ድጋፉ የሚከናወንባቸው አግባቦች ናቸው።

## 8. የተፈጻሚነት ወሰን

ÃI የስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ›ðéçU T’<ªM በሁሉም ክልሎችእና ከተማ አስተዳደሮች ፀድቆ በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባራዊ ይሆናል::

## 9. ማኑዋል ስለማሻሻል

ይህ ማኑዋል እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ካቢኔ/መስተዳድር ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል።

## 10. ማኑዋሉስለሚጸናበትሁኔታ

ይህ የስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ›ðéçUማኑዋል በልዩ ሁኔታ በክልሉ ካቢኔ/መስተዳድር ምክር ቤት ታይቶ ከጸደቀበት ከዛሬ-------------------ቀን-------------------- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

| ቅጽ 001 የተመዘገቡ ስራ ፈላጊዎች ሪፖርት ማድረጊያ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የክልል ስም/ከተማ አስተዳደር | አጠቃላይ የተመዘገቡ ስራ ፈላጊዎች | | | | | | | | | ከተመዘገቡት ውስጥ የምሩቃን ብዛት | | | | | | | | |
| | | 18-34 ዕድሜ | | | 35-60 ዕድሜ | | | አጠቃላይ ስራ ፈላጊ ድምር | | | ዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች | | | የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች | | | ጠቅላላ ምሩቃን ድምር | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ትግራይ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | አፋር | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ኢት.ሱማሌ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | ቤ/ጉ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | ደቡብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | ሐረሪ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 10 | አ.አ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 11 | ድሬደዋ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | **ድምር** | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | |
|---|---|
| **ያዘጋጀው ባለሙያ ስም** | **ያጸደቀው ሀላፊ ስም** |
| **ፊርማ** | **ፊርማ** |
| **ቀን** | **ቀን** |

| ቅጽ 003 አጫጭር የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና ሪፖርት ማድረጊያ | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የክልል ስም/ከተማ አስተዳደር | የቴክኒክ ስልጠና ተጠቃሚ የሆኑ ብዛት | | | | | | | | |
| | | 18-34 ዕድሜ | | | 35-60 ዕድሜ | | | አጠቃላይ ድምር | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ትግራይ | | | | | | | | | |
| 2 | አፋር | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | |
| 4 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | |
| 5 | ኢት.ሱማሌ | | | | | | | | | |
| 6 | ቤ/ጉ | | | | | | | | | |
| 7 | ደቡብ | | | | | | | | | |
| 8 | ሐረሪ | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | |
| 10 | አ.አ | | | | | | | | | |
| 11 | ድሬደዋ | | | | | | | | | |
| | **ድምር** | | | | | | | | | |

| | |
|---|---|
| **ያዘጋጀው ባለሙያ ስም** | **ያጸደቀው ሀላፊ ስም** |
| **ፊርማ** | **ፊርማ** |
| **ቀን** | **ቀን** |

## ቅጽ 004 የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ሪፖርት ማድረጊያ

| ተ.ቁ | የክልል ስም/ከተማ አስተዳደር | ከ 18-34 ዕድሜ | | | | ከ 35-60 ዕድሜ | | | | አጠቃላይ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች | አባላት ብዛት | | | የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች | አባላት ብዛት | | | የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ድምር | አባላት ብዛት ድምር | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ትግራይ | | | | | | | | | | | | |
| 2 | አፋር | | | | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ኢት.ሱማሌ | | | | | | | | | | | | |
| 6 | ቤ/ጉ | | | | | | | | | | | | |
| 7 | ደቡብ | | | | | | | | | | | | |
| 8 | ሐረሪ | | | | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | | | | |
| 10 | አ.አ | | | | | | | | | | | | |
| 11 | ድሬደዋ | | | | | | | | | | | | |
| | **ድምር** | | | | | | | | | | | | |

| | |
|---|---|
| **ያዘጋጀው ባለሙያ ስም** | **ያጸደቀው ሀላፊ ስም** |
| **ፊርማ** | **ፊርማ** |

## ቅጽ 006 የመረጃና ምክር ሪፖርት ማድረጊያ

| ተ.ቁ | የክልል ስም/ከተማ አስተዳደር | መረጃና ምክር የወሰዱ ተጠቃሚ ብዛት | | | | | | አጠቃላይ መረጃና ምክር የወሰዱ ተጠቃሚ ብዛት ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕድሜ 18-34 | | | ዕድሜ 35-60 | | | | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ትግራይ | | | | | | | | | |
| 2 | አፋር | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | |
| 4 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | |
| 5 | ኢት.ሱማሌ | | | | | | | | | |
| 6 | ቤ/ጉ | | | | | | | | | |
| 7 | ደቡብ | | | | | | | | | |
| 8 | ሐረሪ | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | |
| 10 | አ.አ | | | | | | | | | |
| 11 | ድሬደዋ | | | | | | | | | |
| | **ድምር** | | | | | | | | | |

| | |
|---|---|
| **ያዘጋጀው ባለሙያ ስም** | **ያጸደቀው ሀላፊ ስም** |
| **ፊርማ** | **ፊርማ** |
| **ቀን** | **ቀን** |

